የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ግንቦት ፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No.50
Addis Ababa 11th May, 2022

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፩፻፳፯/፪ሺ፲፬
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የኮንስትራክሽን ዲዛይን፣ ግንባታና ማማከር
ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ
ገፅ.............................................፪ሺ፫፻፹

**Regulation Number 127/2022**
**The Addis Ababa City Government Design, Construction, and Consultation Enterprise Establishment Regulation**
Smuggling Of Persons .........Page2380

## ደንብ ቁጥር ፩፻፳፯/፪ሺ፲፬

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮንስትራክሽን ዲዛይን፣ ግንባታና ማማከር ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ

በከተማው እያደገ የመጣውን የቤትና የመሠረተ ልማት ሥራዎች ግንባታ፣ የዲዛይን ዝግጅት እና የማማከር ፍላጎትን ለማርካት፤ በከተማ አስተዳደሩና በተለያዩ ቦታዎች የሚገነቡ ማንኛውንም የግንባታ ፕሮጀክቶችን በዘመናዊ ዲዛይን፣ በጥራት፣ በተመጣጣኝ ዋጋና በተቀመጠለት ጊዜ በመገንባት እያደገ የመጣውን የህዝብ ፍላጎት ምላሽ የሚሰጥና በራሱ ገቢ የሚተዳደር የከተማው አስተዳደር የኮንስትራክሽን ዲዛይን፣ ግንባታና ማማከር ድርጅት ማቋቋም በማስፈለጉ፤

## Regulation Number 127/2022

## The Addis Ababa City Government Design, Construction, and Consultation Enterprise Establishment Regulation

**WHEREAS,** it has been found necessary to establish a design, construction, and consultation enterprise of the city government that runs its own business and responds to the growing demand of the public interest by undertaking the construction of quality, and affordable projects using modern designs and within the specified period which are being constructed by the city government in various areas in order to address the increasing housing and infrastructure works design preparation, construction, and consultation demand in the city;

የአንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፰
Addis Negari Gazeta P.O.Box

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሠን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፸፬/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፹፭ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና አንቀጽ ፺ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮንስትራክሽን ዲዛይን ግንባታ ማማከር ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፩፻፳፯/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **መቋቋም**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮንስትራክሽን ዲዛይን፣ ግንባታና ማማከር ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው የከተማው አስተዳደር የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. የድርጅቱ ተጠሪነት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዲዛይንና ግንባታ ቢሮ ይሆናል፤

፫. ድርጅቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን እና የተወሰኑ የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም በወጣው ደንብ ቁጥር ፲፬/፲፱፻፺፩ መሰረት ይተዳደራል፡፡

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Sub-Article (4) of Article 85 and Article 90 of the Addis Ababa city government executive organs establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation No.74/2021, the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as: "The Addis Ababa City Government Design, Construction, and Consultation Enterprise Establishment Regulation Number 127/2022".

2. **Establishment**

1. The Addis Ababa City Government Design, Construction, and Consultation Enterprise (hereinafter the **"Enterprise"**) is hereby established, having a legal personality, as a public enterprise of the city government by this Regulation;
2. The Enterprise shall be accountable to the Design and Construction Bureau of the City;
3. The Enterprise shall be governed by Regulation No. 14/1998 which provides for the administration of public enterprises of the Addis Ababa City Government and the establishment of the thereof.

## ፫ ዓላማዎች

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩. ማንኛውም ዓይነት የሕንጻ እና የግንባታ ሥራ ፕሮጀክቶችን ዲዛይን ማዘጋጀትና ማማከር፤

፪. ለዲዛይን እና ግንባታ ቁጥጥር የሚያስፈልጉ ደረጃዎች ዝግጅት አገልግሎት መስጠት፤

፫. ለቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያግዙ የዲዛይን፣ ሱፐርቪዥን እና መሰል አገልግሎቶች ላይ የምክር አገልግሎት መስጠት፤

፬. በግንባታ ዘርፍ የዲዛይንና የማማከር ስራዎችን በሚመለከት የጨረታ ሰነድና ውል በማዘጋጀት ከሚመለከተው አካል ጋር አማካሪዎችን እና ተቋራጮችን የመምረጥ አገልግሎት መስጠት፤

፭. ማንኛውንም የግንባታ ፕሮጀክቶችን በጥራት፣ በተመጣጣኝ ዋጋና በተቀመጠለት ጊዜ መገንባት ፣ ማሻሻል እና መጠገን፤

፮. የግንባታ መሳሪያዎችንና ማሽነሪዎችን ማከራየት፣ የግንባታ ግብአት ማምረት እና መሸጥ፤

፯.ለድርጅቱ ልማትና እድገት የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው አይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የምርምር፣ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት በውድድር መንፈስ እንዲሰራ ማስቻል፤

፰.በቤት ግንባታና ተጓዳኝ የግንባታ ዘርፉ ስራዎች የሚታዩትን የግንባታ የማስፈጸም አቅምና የቴክኖሎጅ አጠቃቀም ክፍተቶችን መሙላት፤

፱. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሌሎች ተዛማጅ ፕሮጀክቶች መስራት፡፡

## 3. Objectives

The following are the establishment objectives of the enterprise:

1. prepare any type of building and construction work projects designs and consult the thereof;
2. provide standard preparation service that are needed for design and construction supervision purpose;
3. provide consultation service on designing, supervision, and related services that helps technology transition;
4. provide consultants and contractors selection service together with the concerned organs through preparing tender notices and contracts that are related with designing and consultation works in the construction sector;
5. construct, improve, and restore any construction project without compromising quality, in affordable price, and within the specified period;
6. lease construction materials and machineries; produce and sell construction inputs;
7. ensure that it works in a competitive manner with the relevant research, educational, and training institutions to obtain a well trained manpower in kind, number, and quality for the development and growth of the enterprise;
8. address the construction execution capacity and technology utilization gaps that are exhibited in the housing construction and relate construction section works;
9. carry out other related projects that help to attain its objectives.

፬. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮ የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

፭. **ዋና መስሪያ ቤት**

የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ይሆናል፡፡

፮. **ካፒታል**

ለድርጅቱ የተፈቀደው ጠቅላላ ካፒታል ፫ ቢሊዮን ብር (ሶስት ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፮፻፵፰ ሚሊዮን ፶ሺ.፩፻፶፰ ከ፸፪ ሣንቲም (ስድስት መቶ አርባ ስምንት ሚሊዮን አምሳ ሺህ አንድ መቶ ሀምሳ ስምንት ብር ከሰባ ሁለት ሳንቲም) በጥሬ ገንዘብና ብር ፻፩ሚሊዮን ፱፻፵፱,ሺ. ፰፻፵፩.፳፯ (አንድ መቶ አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ አርባ አንድ ብር ከሃያ ሰባት ሳንቲም) በዓይነት ተከፍሏል፡፡

፯. **ኃላፊነት**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፰. **ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው፡፡

፱. **የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ኢንተርፕራይዝ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል፡፡

4. **Regulatory Authority**

The Addis Ababa city government Finance Bureau shall be the regulatory body of the enterprise.

5. **Main Office**

Addis Ababa shall be the seat of the main office of the enterprise.

6. **Capital**

The authorized capital for the Enterprise is birr 3,000,000,000.00 (three billion birr); of which birr 648,050,158.72 (six hundred forty eight million fifty thousand one hundred fifty eight birr and seventy two cents) is paid up in cash, and birr 101,949,841.27 (one hundred one million nine hundred forty nine thousand eight hundred forty one birr and twenty seven cents) is paid up in kind.

7. **Liability**

The Enterprise shall not be liable beyond its total asset.

8. **Duration of the Enterprise**

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. **Transfer of Rights and Obligations**

The Rights and Obligations of the Construction Enterprise of the Addis Ababa City Government are hereby transferred to the Enterprise by this Regulation.

፪ሺ፫፻፹፬

**፲. ክልከላ**

ድርጅቱ ማንኛውንም የፕሮጀክት ሥራዎችን ለመሥራት ሲዋዋል በአንድ ፕሮጀክት ስራ ላይ የማማከርና የመገንባት ወይም የማማከርና ዲዛይን የመሥራት ሥራ አጣምሮ መሥራት የለበትም፡፡

**፲፩. የተሻረ ሕግ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፩፻፲፭/፪ሺ፲፫ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

**፲፪. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከግንቦት ፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

10. **Prohibition**

The Enterprise When contracting any project, it should not be a combined work of consulting and building or consulting and designing a project.

11. **Inapplicable Law**

The Addis Ababa city government construction enterprise establishment Regulation number 115/2019 is repealed by this Regulation.

12. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of this 11th day of May 2022.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of May 2022.**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**